# የሞት ጉራማይሌ

(ከአብርሃም በየነ)

በማዳበሪያ መርዝ፣ ተበክሎ አፈሩ፣
በሞት ጥላ ግርዶሽ፣ ተከልሎ ምድሩ፣
እንደ ቅጠል ሲረግፍ፣ በላዩ ፍጥረቱ፣
የሞት ሳል ይስላል፣ እንደ ሰው መሬቱ።
ወልቃይት፣ ጠገዴን፣ ቆቦን እያረሰ፣
ዘር አዝርቶ ትግሬ፣ ምርቱን እያፈሰ፣
አማራን ይለዋል፣ "ሞተ በሰበሰ"፣
መሞቱንስ ይሙት፣ ዘር ከበሰበሰ፣
መብቀሉ ይቀራል፣ አፈር ከለበሰ?
ደግሞ እንደ በርበሬው፣ የሽንኩርቱ ሰብል፣
አዝሙድና አቦስዳው፣ ድንብላል፣ ዝንጅብል፣
አንቀልባው ቀረና፣ ታሽጎ በዘንቢል፣
የልጅ ገበያው ደርቷል፣ ዓለም ጉድ እስከሚል።
አገሯ ተዋርዳ፣ በድህነት ታንቃ፣
እንደ ለሙ መሬት፣ እንደ ወርቁ ዶቃ፣
እቱም ገበያ ወጣች፣ ልትሸጥ እንደ ዕቃ።
ንቅሳት ይመስል፣ የሞት ጉራማይሌ፣
ይህ ሄደ፣ ያ መጣ፣ ላላፍ ከገሌ፣
ገኘሁው ከርሃብ ጋር፣ እየተደባዬ
በየ አሥርት ዓመቱ፣ ሳይጨርሰን ብዬ፣
ተማፅኘው ነበር፣ ቢያድነን ተስዬ፣
ምህረት የነፈገን፣ ፍርዱን ያዘገዬ፣

**ይሰማል ወይ እግዜር፣ አረ እናንተ ሆዬ!!!**

(ጥር 2002)